# ድሉ፤ የትጥቅ፣ የስንቅ ወይስ የብዕር ሥም

## አቦ አራዳ አባ ሻውል (EE)

ሚያዚያ ፲ ቀን ፪ሺ፲ህ፰ ዓ/ም

እ.አ. ሚያዝያ 13  2016

## መግቢያ

ይህ ጽሑፍ በአለፈው ሁለት ቅዳሜ በማርያም ቤት ክርስቲያን ተገኝቼ  አንድ በርቁ የማውቀው ግለሰብ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶን፤ ስለ ፍትሐትና የቀብር ሥነ ስርዓት ያየሁት፣ የተገነዘብኩትና የሰማሁትን ለአንባቢዎቼ መልዕክት አዘል መልክት ለማቅረብ ነበር፡፡ ሰውየው ዘለዓለም ብርሃኑ ይባላል፡፡ የትግል ሥሙ ግን **“ድሉ”** ይባል ነበር፡፡ ***ድሉ ዘለዓለም ብርሃኑ፤*** ሥም መልአክ ያወጠዋል እንዲሉ፡፡

ዘለዓለም የሚለው ሥም ወላጆቹ ያወጡለት ሥም ሲሆን የአባቱ ሥም ደግሞ ብርሃን፤ የትግል ሥያሜው ደግሞ ድሉ ነበር ብዬ ከላይ ገልጨዋለሁ፡፡ **“ነበር”** ያልኩበት ምክንያት የዛሬ ሁለት ሣምንት ስለተቀበረ ነው፡፡ ስለሞቱ ቄሱ ሲያስረዱ ዘለዓለም ሞትን አቸንፎ ሄደዋል ብለዋል፡፡ እውነትም ቄሱ ሞትን ማቸነፉ እንዴት አወቁ፡፡ በሕይወት እያለ እንደተሰቃየ ገብተዋቸው ነው ወይስ ሞት ማቸነፍ ነው ብለው ሲለሚያምኑ ነው? አብረን  እንመራመርበት፡፡

## ፍትሐትና ቀብር

የዘዓአለም ፍትሐት ያስፈለገበት ምክንያት የተወለደበትና ያደገበት ባሕል ስለሆነ ይመስለኛል፡፡ የድሉ ቀብር ደግሞ የግዴታ ውዴታ ስለሆነ ነው፡፡ ለመሆኑ በዚህ ወቅት እነማን ተገኙ፤ እንደ ድሉ የመሳሰሉ በዛን ዘመን እንደእሱ ወጣት ሆነው ኢሕአፓን የተቀላቀሉ ነበሩ፡፡ ትኩር ብሎ ለሚያያቸው ሁሉ በአዕምሮ የበሰሉ፣ በአካል የጠነከሩ፤ በውስጣቸው ግን ያረሩ ይመስላሉ፡፡ በግል ኑሮዋቸው የተደሰቱ ነገር ግን በሕዝብ ጉዳይ ላይ ያልተደሰቱ መሆናቸውን ለማንም ግልፅ ነበር፡፡ ለምሳሌ ጓድ ድሉ እንደ ባጎላችን ቢሆን ኖሮ በተወለደበት ሥፍራ በዘጌ መቀበር ነበረበት፡፡ ዝጌ ከአምሰቱ የጣና ባሕርን ጠረፍ አካልለው ካሉ አንድዋ ከተማ ነች፡፡ ለላይኛው የእግዚ -አብ-ብሔር ሥፍራ ድልድይ በሆነች ነበር፡፡ የድሉ ፍትሐተ-ቀብር እዛው ዘጌ መከናወን ነበረበት፤ ግን አልሆነም ምክንያቱም የዘለዓለም ፓርቲ፤ ኢሕአፓ ድል አላደረገም ትሉ ይሆናል፡፡ድል ማለት እንደተርጓሚው ስለሆነ ፈፅሞ አይደለም፡፡

የዘለዓለም ኑዛዜ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፍትሕና ርትዕ ካልነገሠ በሕወትም በሞትም አልገባም ከሚሉ ወገን ስለነበረ ነው፡፡ የድሉ ትርጉምና ሥም ከራሱ የመነጨ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያ ነግሰዋል ማለትም ከደርግ መውደቅ በኋላ የሚሉ በብዛት እንደነበሩና አሁንም እንዳአሉ የታወቀ ነው፡፡ ራሳቸውን ለማታለል፤ ጥቅም ለማግኘት ወይንም የአብዮት ትግልና ፖለቲካ ያልገባቸው ሊሆን ይችላል፡፡ አሁን ግን የነድሉ ትግልና ውጤት በተግባር እየታየ መሆኑን ብንገነዘብ ጥሩ ይመስለኛል፡፡

***ብዙ ሕዝብ ኢሕአፓ ከየት? ወዴት? እንደተጓዘ አለማወቃቸው ብቻ ሳይሆን እንዴት እንደተጓዘና ወዴት አቅጣጫ እንደሚሄድ ባለመገንዘባቸው፤ ረጂምና መራራ ኑሮ እንዲኖሩ እየተገደዱ ናቸው፡፡ ሰደት አንዱ መግለጫው ነው፡፡***

ለምሳሌ ጌታቸው ጀቤሳ (የትግል ሥም) በቅርብ ቀን በጻፈው ጽሑፍ ምስክርነት ወልቃይት፤ጠገዴና ጠለምት፤ እኔ - ATM - አሲመባ-ጠለምትና መርካቶ፤  እያልኩ በእንግሊዘኛ ከምጽፈው የሚለይ አይደለም፡፡ግለሰቡ በተፈጥሮው (ኮከቡ)

ፍትሕን ስለሚያሳድድ ዴሞክራሲያ በሌለበት አገር ፍትሕን ስለሚሻ መረጋጋት የለውም፡፡ እኔም የለኝም፡፡ የእኔው ዴሞክራሲያዊ አለመረጋጋት የተጋራሁት በተፈጥሮ ሳይሆን በኑሮና በትምህርት መሆኑ ነው፡፡

የኢሕፓና የወያኔ ትንንቅ የተገለጠው ወይም እየተጋለጠ ያለው ***<u>በወልቃየት-ጠለምትና ጠገዴ</u>*** እንደዚሁም **<u>በአሲምባ-ጠለምትና መርካቶ</u>** የነበረ የታሪክ ክስተት ነው፡፡ ከዚሁ በዘለቀ ደግሞ ልዩነታቸው በኤርትራ የቅኝ ግዛት መርሆ በሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ጥልቅ የትግል፤ የአዕምሮዊና ባሕላዊ ታሪክ ያዘለ ስለሆነ በቀላሉ የሚፈታ አለመሆኑን ነው፡፡ በትክክለኛውና ታላቁ የኤትዮጵያ አብዮት ደባ ተሰርተዋል፡፡ መሳሳታቸውን በባድሜ ሰበብ አስባብ ገልፀውታልና ይቅር ይበላቸው፡፡ ፀፀት ወይንም ይቅርታ በከንቱ ከሙቶ ሺ በላይ ለሞትባቸው ቤተሰብ ማለቴ ነው፡፡

በነገራችን አቶ ዘላዓለም በመድኅኔ ዓለም  የኤርትራውያን ኦርቶዶክሳዊ ቤተ-ክርስቲያን መፈታት ይችል ነበር፡፡ የሚኖርበት ሰፈር ቅርቡ ብቻ በመሆኑ ሳይሆን ብዙ ኤርትራውያን ጓደኞቹ ነበሩት፡፡ ለነገሩ እዛም ቢፈታ ኖሮ ዘጌም ሄዶ ሊቀበር አይችልም የሚሉ አሉ፡፡ ለምን ቢባል መድኃኔ ዓለም የፈታው ሬሳ አገር ቤት ያለው መንግሥት አይቀበለውምና ነው፡፡ እንደተረዳሁት በኦርቶዶክስ ማርያምና በመዱኃኔ ዓለሙ ክርስቲያናትም ስምምነት የለም ማለት ነው፡፡ ወይ ጊዜ! ታዲያ ጴንጤዎች አቸነፉ ወይስ አሸነፉ ነው የሚባሉ። ይኸ ማለት በኢትዮጵያ ቅድስት ማርያም ዋሽንግተን የሚገኝ እና በኦርቶዶክስ መድኃኔ ዓለም የኤርትራውያን አሠራር ትልቅ ቅራኔ ያለ ይመስላል ማለቴ ነው፡፡

የኢሕአፓ ድርጅት ግን የሃይማኖት ጉዳይ ከመሠረቱና ምንጩ ጀምር የሚያስማማ ቅመም ነበረው አሁንም አለው፡፡ እሱም ኢሕአፓ በእናትና በልጅ ልዩነት አያደርግም፡፡ እግዚአብሔር ይማራቸው እንጂ ዘላዓለምስ በማርያም ሆነ በኢየሱስ ተቀባይነት እንዳለው እመሰክራለሁ፡፡ ኢሕአፓና ኢሕአፓዎች በዚሁ በእናትና በልጅ ልዩነት እንደ አለፈው ጊዜ ፀረ አገር አንድነትና ልዩነት በሚል ሰበብ እንዳይከሰሱ እሰጋለሁ፡፡ የጴንጤዎችንና የኦርቶዶክስ ልዩነትና አንድነት በዚሁ በድሉ ሞትና ቀብር የተገለጠልኝ፡፡ መንግሥተ ሰማያት ሊጋድ ዘላዓለም፡፡ በነፃነትና በአርነት ዘላዓለም እንደኖረ እመሰክራለሁ፡፡ የኢሕአፓ ድርጅት በሃይማኖት፣በሞራልና በአስተሳሰብ ልዩነትና አንድነት እንዳለ በሚገባ ያውቀዋል፡፡ በሌላ አነጋገር በንጉሡ ዘርዓ ያቆብና በፈላስፋው ዘርዓ ያዕቆብ መካከል የኖረውንና የሚኖረውን መስመር ይለያሉ፡፡

## ኢሕአፓና ድሉ

ከላይ እንደገለጥኩት ኢሕአፓ ማለት የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝባዊና አብዮታዊ ፓርቲ ነው፡፡የተቋቋመውም ከዛሬ ዓርባ ዓመታት በፊት ነው፡ ታዲያ ድል አድርገዋል ወይስ ገና ነው የሚል ጥያቄ እንደሚያስከትል ይገባኛል፡፡ እዘህ ላይ እንግዲህ የድሉ ጉዳይ ይነሳል፡፡ ድሉ (ዘለዓለም) ከዝጌ ነኛም ክፍለ-ሀገር ተወልዶ በአብዮታዊ  አመፅ ተመስጦ ከፋሽታዊ ደርግ ካራ አምልጦ ወደ ኢሕአፓ ድርጅት ተቀላቀለ፡፡ በዛች ሰዓትና ቀን ሞትን አቸንፋታል፡፡ ኢሕአፓን የሚቀላቀል ሰው ሠይጣንን ብቻ ሳይሆን መልአክንም ማቸነፍ ነበረበት አሁንም አለበት፡፡ምክንያቱም ድሉ የእግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን የሕዝብም ጭምር ነውና ነው፡፡ የኢሕአፓ ድርጅት የሚታገለው ለአባሎቹና ለደጋፊዎቹ ብቻ ሳይሆን ለአጠቃላይ ሕዝብ ነበር፤ አሁንም እንዲሁ፡፡ ስለሆነም ኢሕአፓዎች ለዚች ዓለም ብቻ ሳይሆን ለምጪው ዓለምም ጭምር ነው፡፡ የዛሬ ወጣቶች ልብ ቢሉ መጪው ዓለም ማለት ለትውልድ ማለትም በእንግሊዘኛ ፖስተሪቲ (Posteriy) ይሉታል፡፡ የኢሕአፓና የትውልደ-ኢሕአፓ ሳይወልዱ፤ ሳይጫወቱ የወጣት ጊዚያቸው መስዋዕት አድርገው አልፈዋል እያለፉም ናቸው፡፡ ዘላዓለምም እንደ ጋዶቹ ለዚችና ለመጪው ዓለም  ሙሉ ዋጋ ከፍለዋል፡ ድል የሚባለው ግና የአሁኑ ወጣት ሊገነዘበው አልቻለም ምክንያቱም ብዙ ውጅምብርና ውሸት ስለነገሡ ነው፡፡እንዴት እንደሆነ ላብራራ፡፡

- የዘውድ መንግሥት በኤትዮጵያ ሰንደቅ - ባለ ሦስት ቀለማት- ሞአ አንበሳ የሚል አርማና መፎክር አስቀምጠው እኛ ብቻ ነን ገዢዎቻችሁ በማለት ከ500 በማይበልጡ የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝብ አርነቱንና መብቱን ለዘመናት ነፍገውታል፡፡ ኢሕአፓም ለዘመናት በሚል መዝሙርና መፈክር ገጥሞ የዘውድ መንግሥት ገልብጦታል፡፡ ሀሰት የሚል ካለ የደብተራው ግጥም **“ቁማር ተጫውቼ”** የሚለውን ይመልከቱ፡፡ በተጨማሪም የላቲን- A- ተገልብጦ ወደ V= volunteerism-vote-victory-በማለት የኢሕአፓ ጽንሐተ-ምሁራን ትልቁ የአፍሪካ አብዮት አካሂደዋል፤ እያካሄዱም ናቸው፡፡ ይህ የተራዘመ የኢትዮጵያ አብዮት በወታደራዊ ደርግ ተጠልፎ ወደ ፋሽስትነት

ተለውጦ እንደገና የኢሕአፓ ትግል ቀጠለ፡፡

- ቀጥሎም ደርግ **(ደብድብ-ርገጥና ግዛ)** ብሎ እኛ ነን ገዥዎቻችሁ ቁጥራችንም 120 ነን በማለት ዋሾቶ ሥልጣን ለሕዝብ እናስረክባለን እያሉ በጉለበት እስከወድቁ እየደበደቡና እየረገጡና ለ17 ዓመታት ገዙ፡፡ ሆኖም የኢሕአፓ ልጆችና ድርጅት እንደ አባቶቻቸው ፋሺዝምና ባንዳነት ሳይበግራቸው ደርግን በጨበጣ ማለት በጽሁፍ፤ በመፎከር፤ በመዝሙር፤ በመታሰር፤ በሞሞትና በወታደራዊ አንቂነት ደርግን ከኢትዮጵያና ኤርትራ ሕዝቦች አግልለውታለ (አጣልተውታል)፡ኢሕአፓ  የደርግ አብዮት ለሕዝብ ምንም ለውጥ እንደማያመጣ እንዲህ ብሎ ተተንብዮ ነበር፤ እንኳን መቶ ሃያ (120) ሆናችሁ መቶ ያ ሺ (12000) ብትሆኑ ለኢትዮጵያ ምንም ቅንጣት ለውጥ እንደማታመጡ ዕወቁት፡፡  ደርግም ይኸንን ያምንበታል፡፡ ዝብርቅርቅ ባለ መሸፋፈን መንግሥቱ፤ፍቅረ ሥላሴና ፍስሓ ደስታ በመጽሓፎቻቸው ገልጠውታል፡፡ በጣም የሚያሳዝነው ጉዳይ ግን በኢሕአፓ አብዮትና በብሔርተኞች ልዩነትና አንድነት ሳያውቁ ማለፋቸው ነው፡፡ ለነገሩስ በጦርነትና በአብዮት ያለውን ልዩነት መቸ አውቀዉት!!!

- አሁን ደግሞ ሰንደቃችሁ ጨርቅ ነው እንዲያውም አንድ ባለ ሦስት ቀለማት ብቻ ሳይሆን በደርዘኖች የሚቆጠር ሰንደቃችሁ ይሁን ብለው በማዘዝ እያሾፉ ዲሞክራሲያ ሰጠናችሁ ይሉናል የሚሉ ነግሠዋል፡፡

ታዲያ ድል ከነዚህ ዓይነት ገዢዎች እንዴት እነ **ድሉ** ድል ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ ድልና ድሉ አብረው ይጋዛሉ፡፡ ቁሱ ድሉ ሞትን ድል አድርገዋል የሚሉት አሁን ሳይሆን ቀድሞውን ወደ ኢሕአፓ ሲቀላቀል ድል ያደረገ ሰው ነው፡፡ ይልቁንስ የዛሬ ስድስት ወር ገደማ ወደ ሆስፒታል ሄደን ስንገበኘው አቶ ድሉ በውድቀተ-እንቅልፍ (ኮማ) ነበር፡፡ ይህንን ውድቀተ-ሞት አልጠቀምውም ትላላችሁ?፤ በበኩሌ ድርብ ድርብርብ ድል ነው እላለሁ፡፡ከምድራዊ ስቃይ ተገላገለ፡፡ የሰማዩ ደግሞ ማን የውቃል?

ኸረ "እናንተ ኢሕአፓዎች ምንድን ነው እኛ ብቻ ነን በዚህ የኢትዮጵያ/ኤርትራ አብዮት ስህተት አልፈፀምን ወደ መንግሥተ ሰማይም እኛው ነን የምንገባው" የምትሉ እንዳላችሁ ይገባኛል፡፡ ሆኖም እውነተኛውን ልንገራችሁ፡፡ ከእኔ ብቻ መስማት ሳይሆን በጽሁፍና ሰነዶች ብትመራመሩ ታገኙታላችሁ፡፡ ስለ ኢሕአፓና ኢሕአፓዎች ብዙ ብዙ ውሸትና አሉባልታ (ፕሮፓጋንዳዎች) ለብዙ ዓመታት ስለተሰራጩ ጉዳዩ ቀላል ላይሆንላችሁ ይችላል፡፡ለምሳሌ ባለፈው ሳምንት አንድ ምሑር ጓደኛዬ ደውሎ የፍስሓ ደስታ መጽሐፍ አነበብከው ወይ ብሎ ጠየቀኝ፤ እኔ ደግሞ ብዙ የሚነበብ የለውም ስለው ከምቅጽበት ኢሕፓዎች እኛ ብቻ ነን ሀቀኞች ትላላችሁ ብሎ ሲነግረኝ ለመጀመሪያ ጊዜ በሕይወቴ ኢሕአፓ ሀቀኛ ነው ብዬ ለመግለጽ ተገደድኩ፡፡ እስከዛሬ  ሀቅ ታሸንፋለች -    Truth will prevail – እያልኩ ነበር በጽሖፎቼ መጨረሻ ላይ የማስቀምጠው፡፡ ይህ ጓደዬ ምሑር ብቻ ሳይሆን ጽንሐተ-ምሑር ብዬ ነበር የፈረጅኩት፤ እሱ እንዲህ ዓይነት አመለካከት ካለው ስንቱ ሕዝብ ነው የተጣመመ በኢሕአፓ ላይ ያለው አመለካከት፡፡ ጉዳዩ ስለአሳሰበኝ እነሆ በአጭሩ ስለ ኢሕአፓ፡-

- ዕምነት
- ዕቅድና
- ዓላማ

ለምግለጽ ልሞክር፡፡

## የኢሕአፓ ዕምነት

ዕምነት ሲባል ለኢሕአፓ የሃይማኖት ጉዳይ አልነበረም፣ አይደለምም፡፡ ዕምነት ማለት መነሻ፤ ማንነትና መታወቂያ በግልም ሆነ

በሕዝብ ዘንድ የሚታወቅ ወይም የሚገለጥ ነው፡፡ ከሃይማኖት ጋር የሚያያዘው የሕዝብ ፍቅር ስለሚያሳይ ነው፡፡ መጽሕፍ ቅዱስም በአብዛኛው በፍቅር የተጠቀለለ ስለሆነ ነው ከኢሕአፓ ጋር ግንኙነት ያለው፡፡ ኢሕአፓ በግል ነቅቶና ተመልምሎ ወደ ፓለቲካ ፓርቲ አባል ይመዘገባል እንጂ ሌሎች ድርጅቶች እንደሚያደርጉት በቡድን በሙዚቃና በግርግር ድርጅቱን አይቀላቀልም፡፡ የድርጅቱ ዋና ሚሥጥር ለብዙኃን የሚገለጥ አልነበረም፡፡ ለነፍሥሓ ደስታ ቀርቶ ለአባላቶቹ እንኳ የማይገለጥ ብዙ ብዙ ሚሥጢር ነበረው፡፡ በሕቡዕ የሚንቀሳቀስ ድርጅት ማንም ለማወቅ አይችልም፡ ዐውቃለሁ የሚል ሰው ከተገኘ ውሸታም መሆኑን መታወቅ አለበት፡፡ ታዲያ በምን ይታወቃል፤ ትክክለኛ ጥያቄ፡፡ የሚታወቀው በዕምነቱ፤በዕቅዱና በዓላማው ብቻ ነው፡፡

## የኢሕአፓ ዕቅድ

የኢሕአፓ ዋና ዕቅድና አሠራር ዲሞክራሲና ዴሞክራሲያ ናቸው፡፡ ትንሹ "ዲ" ለግለሰቡ ሲሆን ትልቁ "ዴ" ደግሞ ለብዙኃኑና ለሠፊው ሕዝብ ነው፡፡ እስከ አሁን ድረስ ለወደፊቱም በዚሁ ስለ ሚቀጥል ኢሕአፓ ትላንትም ዛሬም ነገም አይሳሳትም የሚባለው ለዚሁ ነው፡፡ ይህንን የዲሞና የዴሞ ጉዳይ ዘለዓለማዊ ብርሃን ስለሆነ ነው፡፡ ተፈላጊነቱ ጊዜ የማይሽረው ይሆናል፡፡ ለመሆኑ ዲሞክራሲያ እንዴት ነው የሚሰኘው፤ የኢሕአፓ ሰዎችስ እንዴት አወቁት ለኢትዮጵያውያንና ለኤርትራውያን እንደሚጠቅም፡፡ ጥሩ ጥያቄ ነው፡፡ በምሳሌ ለማስረዳት እንደሚከተለው እገልጸዋለሁ፡፡

የዲሞክራሲያ ንቃት በሦስት መንገድ ይገኛል

- በተፈጥሮ የሚገኝ ዲሞክራሲ፤ ምሳሌ ቢያስፈልግ (ፕረሲደንት ኢሳያስ አፈወርቅ) በወርኃ የካቲት ስለ ተወለደና የአመራር ተፈጥሮ ስለታደለ
- በትምህርት የሚገኝ ዲሞክራሲ፤ ምሳሌ ፕሮፈሰር መስፍን አርአያ በወርኃ ግንቦት ስ ለተወለደና የአመራር ፍላጎት ስለ ተሰጠው
- በኑሮ የሚገኝ ዲሞክረሲ፤ ብዙዎች ኢሕአፓዎች በአካባቢዊ/ENVIRONMENT ስለ ታገሉና ስለ አመኑበት ያገኙት ፀጋ ይሆናል፡፡

የኢሕአፓ ሰዎች በሦስቱም የተሳተፉና የሚሳተፉ ስለሆነ ፅንሰ ሐሳቡና ተግባሩ ከበድ ሳይልባቸው አልቀረም፡፡ በተለይም አመራር ነበርን ወይም ነን ለሚሉ በጣም ከብዶባቸዋል፡፡ ራሳቸውን በዚህ መነጸር ቢያዩት ይጠቅማቸዋል እላላሁ፡፡ *የኤሕአፓ ዋና መርሆና ዕቅድ ዴሞክራሲያ ያለ ገደብ ነበር አሁንም ነው፡፡ ሰፊው ሕዝብ አሁንም መሳተፍ አለበትና፡፡*

ኢሕአፓዎች በሕዝብ ጉዳይ መሳተፋቸው የኖረና የሚኖር ነው፡፡ ተሳትፎአቸው በአርዕስቱ ላይ እንደተገለጠው **በትጥቅ፤በስንቅ ወይንም በብዕር** መሆኑን መታወቅ አለበት፡፡ ድላቸው የሚገመገመው ዓላማና ዕምነት መሠረት ያደረገ ሆኖ በዴሞክራሲያዊ ጽናት ላይ ትኩረት ያደረገ ብቻ ነው፡፡ ዴሞክራሲያዊ ሲባል ኅብረት ነው የኤኮኖሚ መመሪያችን በማለት አወናብደውት አማካሪዎቹ አበረው ወደቁ፡፡ አሁንም ቢሆን በኢትዮጵያና በኤርትራ መንግሥታት የሚያካሂዱት ፕላኒንግ የተደናበረና መረን የለቀቀ ስለሆነ የሕዝብ ጥላቻ እየከረረ ይገኛል፡፡ መፍትሄው ግን አላወቁትም አሊያም አልፈለጉትም፡፡ እንደ ይሁዳ እስካሪዮስ ቢጸጸቱ መልካም ነበር፡፡እኔ በግሌ ይሁዳ የምወደው ሐዋሪያ ነበር፡፡

## የኢሕአፓ ኣላማ

የአሕአፓ ዓላማ ወይም የመጨረሻ ግብ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ/ኤርትራዊ ድምፅ ሰጪ VOTER እንዲሆን ነበር አሁንም ይኸው ነው፡፡ ይህ ሁላ ድርጅት፤ ግለሰቦችና ማኅበራት እኛም አለንበት እንምረተ እያሉ መሰለኝ፡፡ ኢሕአፓ ታዲያ መንገዱና ግቡ ስለአሳየ ለምን ይወቀሳል፡፡ አባቶቻችን ሜዳው ይኸው ፈረሱም ይኸው ብለውን የለ፡፡ መበርታት ነው እንጂ ማንቃሸሽና ማጣጣል ምን ይፈይዳል? የኢሕአፓ ዋና ዓላማ የፖለቲካ ትምህርት ለማቅመስ ነው፡፡ ፖለቲካ ማለት ደግሞ ሌሎች ድርጅቶችና ተራ ግለሰቦች እንደሚሉት ተራ ውሸትና ማጭበርበር ሳይሆን ሣይንሳዊና ርትዓዊ የሆነ መመሪያ ነው፡፡ ፖለቲካ

የሚከሰተው የሕዝብ ግኑኘነት ሲኖር ነው፡፡ ግንኙነት ከሌለ ፖለቲካ የለም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደ ከተሜ ስለሚለወጥ (ጊዜውን ጠብቆ) የግድ ፖለቲካ ስለሚያስፈልግ ተዘጋጅቶ እንዲቆይ ኢሕአፓ ሕዝቡን ለማንቃት የሚበቃው አስተምሯል፡፡ ያስተማረው መንገድ በዴሞክራሲያዊ ዘዴ ስለሆነ ከፈላጭ ቆራጭነት ለማላቀቅ ከባድና ውስብስብ ነበር፡፡ ኢሕአፓና ኢሕአፓዎች፤ ዴሞዎች ተብለው በመፈረጅ ምሑራኖችና (ጸንሀተ-ምሑራን ያልሆኑ ማለቴ ነው) በጅምላ ተገድለዋል፤ታስረዋል፤ተግዘዋልና ደብዛቸው ጠፍተዋል፡፡ ዴሞክራሲያ ግና በስም ደረጃ ዕድሜ ለኢሕአፓ ነግሰዋል፡፡ ኢሕአፓ ይህንን ቃል በኢትዮጵያውያን አፍ ካስፈታ ቀሪው ሥራው ስለ ፖለቲካ ሀ ሁ ማስተማር ይሆናል፡፡ እንደ ደርጎቹ የአብዮት ሚስጢር አካሄድ ሳይገባቸው ቀርቶ ይሁን ወይንም ሆን ብለው ለራሰቸውም ሳይሆኑ ብዙ ውድቀት እንዳመጡ ሁሉ አሁንም የሻዕቢያም ሆነ የወያኔ መንግሥታት ፖለቲካ አያስፈልግም በማለት ብዙ ውድቀት እያሳዩ ስለሆነ ከአሁኑ ስለ የፖለቲካ ሁላችን መማማር ይኖርብናል፡፡ ዕድሉ ሠፊ ነው፡፡ ይህ ማለት በአገራችን ብቻ ሳይሆን በተሰደድንበት አኽጉራት ጭምር ማለቴ ነው፡፡ እንዳልኩት በአገራችን ከተሜነት -Urbaniztion- ገና ዳዴ እያለ ነው፡፡ የኢሕአፓ ፖለቲካ የግንኙነት ጉዳይ ነው፡፡ ሁላችንም በአገራችን ድምፅ ሰጪ መሆን አለብን፡፡

## የድሉ ሞት የኢሕአፓ ሞት ወይስ ትንሣኤ

ድሉ ማነው ኢሕአፓስ ማነው የዘመኑ ወጣት ጥያቄዎች እንደሚሆን አልጠራጠርም፡፡ ድል ወይም ዓወት ፅንሰ-ሐሳብ እንደመሆኑ መጠን የትግል ውጤትም ይህው ነው፡፡ኢሕአፓና ድል መቸ ተገናኝተው?ኢሕአፓ ከሞተ ቆይተዋል ይባል የለ እንዴ? ደግሞ ኢሕአፓ የፖለቲካ ድርጅት ነው፤ ፖለቲካ ደግሞ ሞት የለውም፡፡ ታዲያ ምን አገኛቸው፤ መልሱ እንደሚከተለው እገልፀዋለሁ፡፡

ይኸን ሁላ ካልኩ በኃላ፣ ሥነ ሥርአቱ እንዴት አለቀ፡፡ ከቀብሩ በኃላ ኢሕአፓና ኢሕአፓዎች በቅድሥት ማርያም ቅጠር ግቢ በመምጣት ተሰባስበው ጠበል ፅዲቁ ወይም ምሳቸውን በሉ፡፡ አሰላለፋቸው በምዕራብ በኩል በሜዳ የተሰለፉ ኢሕአፓዎች፤ በሰሜን ደግሞ የከተሜ ኢሕአፓዎች ሲሆን በደቡብ ወገን ደግሞ በአሁኑ ጊዜ ድርጅቱን የሚመሩ አባላት ነበሩ፡፡ በምስራቅ ወገን ግን ማንም የለም ነበር፡፡ ምናልባት መረሻ ዮሴፍ ነበር በመንፈስ እላለሁ፡፤ የመርሻ አመራር ከተነሳ እንደሚከተለው ነው የምመለከተው፡፡ መርሻ የሴፍ የተወለደው በወርሃ ነሐሴ ነው፡፡ ይህ ማለት እንደነ ኃይለ ሥላሴ በአንበሳነት ይፈረጃል፡፡ ሆኖም እኛ አገር ሥርዓት ገና ያለነገሠ፤ ንጉሥ የማያስፈልግበት ጊዜ ስለሆነ በተለይም እነ መርሻ የንግሥነት ስርዓት ተታግለው ስለጣሉት የሚመለስ አለመሆኑን መገንዘብ ያሻል፡፡ ታዲያ ከአመራር አንዱ አባል በመሆን መታገል እንጂ በአምባገናናነት መምራት ከእንግዲህ ወዲያ አይቻልም፡፡ ሌላ ድርጅት መሥርቶ ለዛውም ተመሳሳይ ዓርማና ታሪክ ተሞርክዘው መታገል የሚቻል አልሆነም፡፡ጊዜው እንኳን ሰው **ነፋስንም መስማት ብቻ ሳይሆን ማየትና መጨበት ስለተቻለ ነው፡፡ ስለ ነፋስና አመራር ከተነሳ አይቀር ኢያሱ ዓለማየሁ በወርኃ ሰኔ ስለተወለደ ከአመራር ምድብ አይደለም፤ እሱ ከዕውቀት ምድብ (ግሩፕ) ነው፡፡**

ታዲያ ለምን አመራሮቹ አይስማሙም ተብሎ ሲጠየቅ፤ መልሱ ቀላል ነው፡፡ ከላይ እንደተገለጠው በዕምነትና በዓለማ ይስማማሉ፡፡ የማይስማሙበት ጉዳይ በዕቅድ ማለት ዲሞክራሲያና ዴሞክራሲያ ግንዛቤና አካሄድ ብቻ ነው፡፡ አሜሪካኖች ልዩነታቸው የሚያስወግዱት በአርና በዴሞ ወይንም በዝሆንና በአህያ ዓርማና መፎክር ነው፡፡ በኢሕአፓ(ዲ)ና በኢሕአፓ (ዴ) ዓርማና ዜማ ምንም ልዩነት የለውም፡፡ ልዩነት ካለ በምርጫ የሚወገድ ነው እንጂ በመካሰስ አልነበረም፡፡ አሁንም ቢሆን ከተፈለገ በምርጫ ካልሆነ በኮከብ ምርምር ማድረግ ይቻላል፡፡ በዚሁ በድሉ ሞት ያየሁት መፋቀርና መተሳሰብ አስደስቶኛል፡፡ እንደሚታወቀው በቀብር፣ በሠርግና በፍትሐት የኢሕአፓ ልጆች ብዙ አይታሙም፡፡ በችግርና በኃዘን ጊዜ መገኘት ማን ብሎአቸው፡፡ በዛች ቀን እንደአጋጣሚ ሥራ ስለ አልሠራሁ ነው እኔም ወደ ቅደሥት ማርያም የሄድኩና ሁኔታውን የተከታተልኩ፡፡ እንደ ገመትኩት የድሉ ድል አይቀሬ ነው፡፡የኢሕአፓም ትግልም እውን እንደሚሆን በእርግጠኛነት መተንበይ ይቻላል፡፡ ዓግመላሳ ብላችሁ ከተነሳችሁና የደቡና የፕሮፈሰር መስመር ይገለጥላችሃል፡፡ የመፍትሔ ታሪክና አካሄድ ከእነሱ ዘንድ ይገኛል፡፡

## መደምደሚያ

*የድሉ ኀልፈት-ሥቃይና የተጸውኦ ሥም የኢሕአፓ ድል ብርሃንና ዘለአለማዊ መሆኑን የሚጠቁም ይመስለኛል፡፡ ለዚሁ የተቀደቐሠ ዴሞክራሲያዊና ፖለቲካዊ አካሄድ ወይም ግኑኝነት ብዙ ግለሰቦች በተለይም ከአሲምባ አርበኞች፣ ከጠለምት ጀግኖችና ከመርካቶ ቻምፒዮኖች አግኝተነዋል ለወደፊቱም እንደምናገኝ መተማመን አለብን፡፡*